| የአፈጻጸም ብቃት ዓላማ | ስትራቴጂዎች | መሪ ጠቋሚዎች<br>(ለውጥን ለመከታተል ጥቅም ላይ የሚውሉ) | የኋላ ጠቋሚዎች<br>(ለአመቱ መጨረሻ ሪፖርት ጥቅም ላይ የሚውሉ) | ቁልፍ የብቃት አመላካቾች |
|---|---|---|---|---|
| ቅድሚያ የሚሰጠው 1፡ የተማሪ አካዳሚያዊ እድገት እና ስኬት<br>APS ከፍተኛ ጥራት ባላቸው ትምህርቶች እና የድጋፍ ስርዓቶች ተጠቅሞ የዕድል እና የስኬት ክፍተቶችን **በማስወገድ** እያንዳንዱ ተማሪ አካዳሚያዊ ልህቀት እንዲያስመዘግብ ስራ ይሰራል። | | | | |
| • በ 2030, ቢያንስ 85% የሚሆኑት የ APS ተማሪዎች የ Virginia Standards of Learning (SOL's) (ቨርጂኒያ የትምህርት ደረጃዎች) ግምገማዎችን የብቃት መስፈቶችን ያሟላል ወይም አልፎ ይሄዳል እንደዚሁም ሁሉም የሪፖርት ቡድኖች የ APS የልህቀት ክፍተቶችን ለመዝጋት የወጡ ዓመታዊ ዓላማዎችን ያሟላሉ ወይም እነዚህን አልፈው ይሄዳሉ። | • ከቨርጂኒያ የትምህርት አሰጣጥ ደረጃ ጋር የተጣጣመ ጥብቅ፣ ልዩነትን በሚያከብር፣ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ እና ባህልን የሚያከብር የትምህርት አሰጣጥ በኩል በ APS ስራ ላይ የዋለ የትምህርት ስርዓት ማቅረብ።<br>• በታሪክ በተገለሉ የተማሪ ቡድኖች ላይ በግልጽ ትኩረት በማድረግ የሁሉንም ተማሪዎች ብቃት ለማሻሻል የሚያስችል ሞያዊ ትምህርት ለ አስተማሪዎች እና ለረዳት አስተማሪዎች መስጠት። እነዚህ ድጋፎች የሚከተሉትን ነገሮች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ያደርጋሉ፡<br>  ○ አድልዎዎችን መቀነስ ወይም ማስወገድ፣<br>  ○ የንባብ ሳይንስ፣<br>  ○ ወሳኝ አስተሳሰብ፣ ፈጠራዊ አስተሳሰብ፣ ትብብር፣ ግንኙነት፣ እና የዜግነት ክህሎቶች<br>  ○ ባህልን የሚያከብሩ የትምህርት አሰጣጥ እና የባህሪ ድጋፍ ልምምዶችን መደገፍ እና ማሻሻል።<br>  ○ አካታች በሆነ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ሁሉንም ተማሪዎች ለማገዝ የሚያስችላቸው ሀብት ላይ መሰረት ያደረገ የችግር አፈታት ለሁሉም አስተማሪዎች።<br>• በሁሉም ትምህርት ቤቶች እና የስራ ክፍሎች ውስጥ የጋራ ቅልጥፍናን ለመገንባት መዋቅሮችን (የሞያዊ ትምህርትማህበረሰቦችን የእቅድ ቀናት, በእቅድ መርሃ ግብር ውስጥ ጊዜን ቅድሚያ መስጠት፣ የጋራ ቋንቋ) ማቅረብ።<br>• በ ከፍተኛ የስራ መልቀቅ መጠን በሚታይባቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ ላሉ መምህራን ማበረታቻ መስጠት (ማለትም ለሙያዊ ትምህርት ተጨማሪ የመልቀቂያ ጊዜ፣ ተጨማሪ ማካካሻ)<br>• በሁለት የምስክር ወረቀት ባላቸው አስተማሪዎች የሚሰጡ በጋራ የሚሰጡ የ ኮርሶች እና ትምህርቶች ክፍሎች እንዲጨምሩ ማድረግ ይህም በሁሉም ደረጃ ላይ የሚገኙ SWD፣ Els እና በጋራ የተለዩ ተማሪዎችን የማካተት ስራን ለመደገፍ ያስችላል። | • ዩኒቨርሳል የሂሳብ ፈተና<br>• ዩኒቨርሳል ማንበብና መፃፍ ፈተና<br>• የትምህርት ዓይነት ላይ መሰረት ያደረገ መሰረታዊ ግምገማ<br>• APS Writing Performance Based Assessment (PBA) (የመጻፍ ብቃት ላይ መሰረት ያደረገ ግምገማ) በ 9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች | • የንባብ SOLs<br>• የመጻፍ SOLs<br>• የሂሳብ SOLs<br>• የሳይንስ SOLs<br>• የማህበራዊ ጥናቶች SOLs | • % የሚሆኑ ተማሪዎች የ 3 ኛ ክፍል የ ንባብ SOLs ያለፉ ሁሉም ተማሪዎች እና በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች<br>• % የሚሆኑ ተማሪዎች የ 8 ኛ ክፍል የ ንባብ SOLs ያለፉ ሁሉም ተማሪዎች እና በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች<br>• % የሚሆኑ ተማሪዎች የ 11 ኛ ክፍል የ ንባብ SOLs ያለፉ ሁሉም ተማሪዎች እና በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች<br>• % የሚሆኑ ተማሪዎች የንባብ SOLs ያለፉ ለሁሉም ተማሪዎች እና በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች<br>• % የሚሆኑ ተማሪዎች የጽሑፍ SOLs ያለፉ ለሁሉም ተማሪዎች እና በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች<br>• % የሚሆኑ ተማሪዎች የሒሳብ SOLs ያለፉ ለሁሉም ተማሪዎች እና በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች<br>• % የሚሆኑ ተማሪዎች የሳይንስ SOLs ያለፉ ለሁሉም ተማሪዎች እና በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች<br>• % የሚሆኑ ተማሪዎች የማህበራዊ ጥናት SOLs ያለፉ ለሁሉም ተማሪዎች እና በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች |

| የአፈጻጸም ብቃት ዓላማ | ስትራቴጂዎች | መሪ ጠቋሚዎች<br>(ለውጥን ለመከታተል ጥቅም ላይ የሚውሉ) | የኋላ ጠቋሚዎች<br>(ለአመቱ መጨረሻ ሪፖርት ጥቅም ላይ የሚውሉ) | ቁልፍ የብቃት አመላካቾች |
|---|---|---|---|---|
| • እስከ 2030 ባለው ግዜ ውስጥ፣ ቢያንስ 90% የሚሆኑት የ አንደኛ ደረጃ እና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንደዚሁም የ 9 ኛ ክፍል ተማሪዎች በ ሂሳብ እና ንባብ የተቀመጡትን ዓመታዊ የዕድገት ግቦችን ያሟላሉ/ያሳካሉ። | • ሁሉንም አንባቢዎች እና በተለይም ከችሎታ በታች ያሉትን ለማሳደግ ፣ የንባብ ስልቶችን እና የስርዓተ-ትምህርት ሀብቶችን ሳይንስ መተግበር።<br>• በየዓመቱ ክህሎቶችን እና የይዘት ዕውቀትን ለማሻሻል እና የሁሉም ተማሪዎች (ግዜ፣ ዕድል እና የኮርስ ምርጫን ጨምሮ) የተለያዩ ፍላጎቶች ለሟሟላት በሚያስችል መልኩ የንባብ እና የሂሳብ ትምህርቶችን ግላዊ ማድረግ።<br>• ተማሪዎች ከትምህርት እና የግል ፍላጎቶች እና የባህል አግባብነት ጋር የሚጣጣሙ ዕውቀቶች እና ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ ለማስቻል የተፋጠኑ የትምህርት ዕድሎችን ማቅረብ።<br>• በሁለተኛ ደረጃ ጥልቅ ትምህርቶች ያለው ምዝገባ ከ የትምህርት ቤቱ ምዝገባ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ይሄድ ዘንድ፣ ይህን ምዝገባ የተመለከተ መረጃ የሚሰጥ፣ የሚያበረታታ እና የሚከታተል ስርዓት ጥቅም ላይ ማዋል። | • ዩኒቨርሳል የሂሳብ ፈተና<br>• ዩኒቨርሳል ማንበብና መፃፍ ፈተና<br>• DIBELS<br>• የ WIDA ተደራሽነት ለ EL's | • ዩኒቨርሳል የሂሳብ ፈተና<br>• ዩኒቨርሳል ማንበብና መፃፍ ፈተና<br>• DIBELS | • % የሚሆኑት የ አንደኛ ደረጃ፣ የመካከለኛ እና የ 9 ኛ ክፍል ተማሪዎች በየዓመቱ በ NWEA የዕድገት ካርታ ላይ በ ሂሳብ ዕድገት እያሳዩ ያሉ፡<br>  ○ በ ፎል ወቅት መካከለኛ (31-60 ፐርሰንታይል) ውጤት ያመጡ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸው ዕድገት በማሳየት ላይ<br>  ○ ከመካከለኛ ውጤት ደረጃዎች ስኬት በታች ውጤት ያመጡ ተማሪዎች (0-30 ፐርሰንታይል) የተፋጠነ ዕድገት (61 ፐርሰንታይል ወይም ከዚህ በላይ) የሆነ ዕድገት በማሳየት ላይ<br>  ○ የሚለካ መሻሻል እና ከመካከለኛው የውጤት ደረጃ በላይ (61 ፐርሰንታይል ወይም ከዚህ በላይ) የሆነ ውጤትን በቀጣይነት በማምጣት ላይ<br>• % የሚሆኑት የ መካከለኛ ትምህርት ቤት እና የ 9 ኛ ክፍል ተማሪዎች በየዓመቱ በ NWEA MAP ዕድገት ላይ በንባብ ዕድገት እያሳዩ ያሉ፡<br>  ○ *ከላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ መለኪያ*<br>• % የሚሆኑት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች በየዓመቱ በ DIBELS ግምገማ ላይ በንባብ ዕድገት በማሳየት ላይ፡<br>  ○ በክፍል ደረጃ ላይ ላሉ ተማሪዎች በያንስ የአንድ ዓመት ዕድገት በማሳየት ላይ፣ ወይም<br>  ○ ከክፍል ደረጃ በታች ላሉ ተማሪዎች ቢያንስ የአንድ ዓመት ተኩል የሚሆን ዕድገት ማሳየት (በ DIBELS የመሻሻል መለኪያ መሰረት)፣ ወይም<br>  ○ ከ ክፍል ደረጃ በላይ ላሉ ተማሪዎች የሚለካ መሻሻል እና በከፍተኛው ደረጃ ላይ በቀጣይነ ውጤት ማስመዝገብ |

| **የአፈጻጸም ብቃት ዓላማ** | **ስትራቴጂዎች** | **መሪ ጠቋሚዎች**<br>(ለውጥን ለመከታተል ጥቅም ላይ የሚውሉ) | **የኋላ ጠቋሚዎች**<br>(ለአመቱ መጨረሻ ሪፖርት ጥቅም ላይ የሚውሉ) | **ቁልፍ የብቃት አመላካቾች** |
|---|---|---|---|---|
| • እስከ 2030 ባለው ግዜ ውስጥ፣ ቢያንስ 80% የሚሆኑት የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ከትምህርት ቀን ቢያንስ 80% የሚሆነውን ግዜ  የአካል ጉዳት ከሌለባቸው በሁሉም ደረጃ ካሉ የትምህርት ቤት ጓደኞቻቸው ጋር በአጠቃላይ የትምህርት ስርዓት ላይ ትምህርታቸውን ይከታተላሉ። | • አካታች በሆኑ የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ውጤታማ የሆነ የጋራ ማስተማር እና የጋር ዕቅድ አወጣጥ እንዲኖር የሚያስችሉ የአካዴሚክ መርሃግብር አቀራረቦችን ማዳበር እና ስራ ላይ ማዋል።<br>• ጥብቅ ማስተማርን ለማሳደግ የሚያስችሉ የ የጋር ዕቅድ እንድ የጋራ ማስተማር ስትራቴጂዎችን ማዳበር እና ስራ ላይ ማዋል። | • % የሚሆኑት የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ቢያንስ 80% የሚሆነውን የትምህርት ቀን በ አጠቃላይ የትምህርት አሰጣጥ ላይ እንዲያሳልፉ<br>• % የሚሆኑት በ SEL የዳሰሳ ጥናት (በራስ መተማመን) “...በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ የተሰጠንን ስራ እንደምናጠናቅቅ እርግጠኞች ነን” የሚል ምላሽ የሰጡ የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች።<br>• % የሚሆኑት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የምስክር ወረቀት ያላቸው አስተማሪዎች የሚገኙባቸው አካታች የሆኑ መማሪያ ክፍሎች | • % የሚሆኑት የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ቢያንስ 80% የሚሆነውን የትምህርት ቀን በ አጠቃላይ የትምህርት አሰጣጥ ላይ እንዲያሳልፉ | • % የሚሆኑት የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች ቢያንስ 80% የሚሆነውን የትምህርት ቀን በ አጠቃላይ የትምህርት አሰጣጥ ላይ እንዲያሳልፉ |
| • እስከ 2030 ባለው ግዜ ውስጥ ቢያንስ 95% የሚሆኑት ተመራቂ ተማሪዎች ቢያንስ አንዱን የ ኮሌጅ፣ የስራ፣ የሲቪላዊ ዝግጁነት አመላካቾች (CCCRI) ያሟላሉ። | • ከ 7ኛ ክፍል ጀምሮ፣ የስራ ፍላጎት ግምገማዎችን ጥቅም ላይ በማዋል የተማሪን አካዳሚያዊ ምክር እና የኮርስ/ትምህርት መውሰድ ውሳኔዎችን በተመለከተ መመሪያ መስጠት።<br>• ከመካከለኛ ትምህርት ቤት ጀምሮ ላሉ ተማሪዎች ያሏቸውን ፍላጎቶች፣ አካዳሚያዊ መሻሻል፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያጠኑት ትምህርት እና የምርቃት ዕቅድ ለመገምገም የሚያስችል መደበኛ የሆነ (ቢያንስ በአመት አንዴ) አካዳሚያዊ የምክር አገልግሎት መስጠት።<br>• የሁሉንም ተማሪዎች አካታችነትን፣ መንገዶችን እና እድሎችን ለማንፀባረቅ የሚያስችሉ የሙያ መንገዶችን ማዳበር፣ መተግበር እና እነሱን የተመለከተ መረጃ ማስተላለፍ።<br>• ከፍተኛ ጥራት ያለው ስራ ላይ የተመሰረቱ የመማር ልምዶችን ጨምሮ ተማሪዎች እውቀትን፣ ክህሎቶችን እና የግል ፍላጎቶችን ከሙያ እና ከኮሌጅ እድሎች ጋር ማጣጣም እንዲችሉ በተለያዩ መቼቶች፣ ጊዜያት እና ቅርፀቶች የመማር እድሎችን ማቅረብ። | • # እስከ 8 ኛ ክፍል ድረስ የ 5-ዓመት ዕቅድ ያላቸው ተማሪዎች፣ይህም በተማሪ የብሄር/የዘር ማሳያ ቡድኖች የተከፋፈለ።<br>• #በ እያንዳንዱ ተማሪ የብሄር/የዘር ማሳያ ቡድኖች እና የክፍል ደረጃ እያንዳንዱን የ CCCRI አመልካችን የሚያሳካ ተማሪ | • ለተመራቂ ተማሪዎች ተማሪ የብሄር/የዘር ማሳያ ቡድኖች የCCCRI ማጠናቀቂያ መረጃ | • % የሚሆኑት ተመራቂ ተማሪዎች በ ተማሪዎች ቡድን CCCRI  እንዲያሳኩ |